# ሁሉንም ሞከርነው፤ የቀረን ክተት ነው


**ጌታቸው ኃይሌ**

ghaile1445@gmail.com


***መግቢያ***

*በዚህ ሰሞን ከተለያዩ ኢትዮጵያውያን አፍ የሚሰማውና ከተለያዩ ድርጅቶች ዘንድ የሚወጣው መግለጫ ሁሉ የሚለው ይኸንን ለዛሬው የድርሰቴ ርእስ ያደረግሁት ነው--በኢትዮጵያ የሕዝብን ነፃነት የሚያስከብር ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ለመዘርጋት ግማሽ ምእት ዓመት ያህል ደከምን። ሁሉንም ሞከርነው፤ በተለይ አሁን ሀገሪቷ በትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር* (Tigray People's Liberation Front) *እጅ እስካለች ድረስ ይኼ የሕዝብ ምኞት ሊደረስበት እንደማይቻል የግንቦት* 15 *ቀን* 2002 *ዓ.ም. ምርጫ ውጤት አረጋግጦልናል። ይኸ ዕለት የትግል ስልት ለመለወጥ ወሳኝ ቀን ሆኖልናል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ምኞት እውን ለማድረግ መጀመሪያ በክተት ደረጃ ተባብረን በማንኛውም መንገድ ኢትዮጵያን ከትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ማላቀቅ አለብን የሚል ነው። የኔም የዛሬው ድርሰቴ የቀጣዩን እርምጃ የሚመራ ተጨማሪ ድምፅ ነው።*

*የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አባላት ጓደኞቻቸውን ሳይቀር እየገደሉና የአሞራ ራት እያደረጉ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠሯት ከ*1983 *ዓ.ም. ጀምሮ፥ አራት የሐሰት ምርጫዎች አካሂደዋል። ሁሉም የሐሰት ምርጫዎች ወይም ንጥቂያዎች ሲሆኑ ድብቅ ያልሆነው በልባቸው ያለው ዓላማቸው እንዲህ የሚል ነው፤*

> *በ*97*ቱ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲና ነፃነት ምን እንደሆነ ገና በግልጽ ስላልተረዳ፥ ተሳስቶ ቅንጅትን መረጠ። አሁን ግን እስከ* 2002*ቱ ምርጫ ድረስ በተደረገው የማስተማር* (brain washing) *ከፍተኛ ጥረት ሁሉም ስለተማረ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት እንደማያስፈልገው መስማማቱን በዛሬው በ*2002*ቱ ምርጫ አሳይቷል።* 99.6 *በመቶው ፋሺስታዊ አገዛዛችንን መርቆልናል።*

*ይኸንን ነው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ሊፈጽመው የፈለገው። ባጭሩ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የመድረክና የመኢአድ ደጋፊ ሳይቀር በፈቃዱ ራሱን ከነፃነት ነፃ አውጥቷል። አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞችም "የተቃዋሚዎቹ አድቃቂና መጠን አልባ ሽንፈት"* (a crushing and colossal defeat for the opposition) *ይላሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ሽንፈቱ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር እንጂ የተቃዋሚዎቹ አይደለም። የተቃዋሚ ቡድኖች በ*99.6 *በመቶ ተሸነፉ ማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠላቶቹ ተሸነፈ ማለት ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ "አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ወያኔን ይደግፋል" የሚባለውንም ያስተባብልልናል። የውሸታቸው መጠን አልባነት ደጋፊዎቻቸውን ሳይቀር መፈናፈኛ አሳጥቷቸዋል።*

**የቁጣ አደጋና ጥቅም**

*የተሰማው ውጤት የተቃዋሚ ቡድኖችንና ደጋፊዎቻቸውን አስቆጥቷቸዋል፤ ሊያስቆጣቸው ይገባል። የተቆጣ በደሉን ለማስወገድ ይነሣል። ያልተቆጣ የበደል ራት ሆኖ ይቀራል። ግን አባቶቻችን "ተምዕዑ ወኢተአብሱ" (ተቆጡ ግን ቁጣ እንዳያሳስታችሁ ተጠንቀቁ) የሚሉትን ምክር መርሐዋቸው እንደሚያደርጉት ሙሉ ተስፋ አለኝ። መርሐውን መከተል ጥበብ እንጂ ፍርሃት አይደለም። የደርግንና የወያኔን አፈ ሙዝ ፊት ለፊት የተጋፈጠን፥ የወያኔንና የደርግን እስር ቤቱን ያጣበበን ሕዝብ ፈሪ ማለት ስድብ ነው። እንዲህ ያለ ችግር ሲፈጠር በእርጋታና በጥንቃቄ ካልተያዘ፥ በቤተ ሰብ ውስጥ እንኳን ሳይቀር ብጥብጥ ይፈጠራል። በከፍተኛ ደረጃም ሲደርስ፥*

የተበደሉ ወገኖች በደለኛውን ትተው እርስ በራሳቸው መወነጃጀል፥ ቀጥሎ ሊደረግ የሚገባውን ማሰባቸውን ትተው፥ የማይረባውን "ነግሬህ ነበር፥ ነግሬሽ ነበር" ማለትን ይጀምራሉ፡፡ የሆነው ሌብነት የተቃዋሚ ቡድኖችን የሚያዋጣ የትግል ስልት እንዲያስቡና እንዲያቅዱ የሚያስገድዳቸው ይመስለኛል፡፡ ምን ዓይነት ትግል?

**ምን ዓይነት አማራጭ**

እውን ለማድረግ የምንፈልገው ምኞታችን ምንድን ነው? የክተት ትግልስ የሚዋቀረውና የሚካሄደው እንዴት ነው?

የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከመጨረሻዋ እስትንፋሹና እስከመጨረሻዋ የደም ጠብታው ድረስ የሚታገልለት ምኞቱ ምን እንደሆነ ሳይገለጽ ግልጽ ነው፤ አምላክ የሰጠውንና የቀድሞዎቹ አባቶችና እናቶች ነቅተው የጠበቁትን ነፃነት የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር የሕዝብ ተቆርቋሪ መስሎ ወስዶበታል፡፡ ታፍራና ተከብራ የኖረችውን ሀገሪቷንም ለሌላ ሕዝብ እየቸረቸራት ነው፡፡ ጠላት የሚያካሂደው እንደ መንገድ ሥራ ያለ የእድገት ፕሮጀክትና ለሰዎች የሚሰጠው የጥሬ ገንዘብ ጉቦ የሕዝቡን አፍ ለመለጎም የጠመንጃው አፈ ሙዝ አልበቃህ ቢለው ነው፡፡ በዚያ ላይ ሊፈጽምልን በማይፈልገው "የአደርግላችኋለሁ" ባዶ ተስፋ ይደልለናል፡፡

ሕዝቡ የሚፈልገውና ሊያገኝ የሚገባው አስተዳደር ምን ዓይነት እንደሆነ የተቃዋሚ ቡድኖች ከምርጫው በፊት በአደረጉት ውይይት በኅብረት ግልጽ አድርገው ነግረውናል፡፡ እነሱ እንዳብራሩት፥

> ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ሀገር ስለሆነች፥ ዜጎቿ ለአዲስ ሕይወት፥ ለአዲስ ዘመን በፈለጉት መንገድ ያዋቅሯታል፡፡
>
> ሕዝብ የሚያስተዳድረውን ፓርቲ የመምረጥ ሙሉ ነፃነት መብቱ ነው፤ ምርጫውን የሚያካሂደው ቦርድ ከማንኛውም ተወዳዳሪ ፓርቲ ጋር ግንኙነት አይኖረውም፡፡ ማንኛውም ተወዳዳሪ ፓርቲ ከሌሎች ተወዳዳሪ ፓርቲዎች የበለጠ ወይም ያነሰ በመንግሥት መዋቅርና ሀብት መጠቀም አይችልም፡፡ ገዢው ፓርቲ በመገናኛ ብዙኃኑ ብቸኛ ተጠቃሚ እንዳይሆን ከመንግሥት እጅ ወጥተው ነጋዴዎች እጅ ይገባሉ፡፡ ሐሳብንና ሃይማኖትን በጽሑፍም ሆነ በቃል፥ በስብሰባም ሆነ በተናጠል፥ በመገናኛ ብዙኃንም ሆነ በሰላማዊ ሰልፍ መግለጽ የማያስከስስ የማንም መብት ነው፡፡
>
> ሀገር የምታድገው በግለሰብና በድርጅቶች የግል ጥረት ስለሆነ፥ ጥረታቸው ሕዝብ ሳይጎዳ እንዲቃና መንግሥት መንገዱን ያሳምርላቸዋል፡፡ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጾታ፥ በቀየ፥ በጎጥ፥ በብሔር ሳይዳላባቸው፥ ሁሉም እኩል በንግድ፥ በኢንዱስትሪ፥ በግብርና የመሠማራት መብታቸው እኩል ይጠበቅላቸዋል፡፡ መንግሥትና ፓርቲዎች የገንዘብ ትርፍ የሚያስገኝላቸው ሥራ አይሠሩም፡፡ መንግሥት ባጀቱን ለሀገረ ክፍሎች የሚደለድለው በሚገብሩት ልክ ሳይሆን በሕዝቡ ብዛት ልክ ይሆናል፡፡ ኋላ ቀር ክፍለ ሀገሮች ከሌሎቹ ክፍለ ሀገሮች የሚያስተካክላቸው ተጨማሪ ገንዘብ ይሰጣቸዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አባላት ኢትዮጵያን ሃያ ዓመት ያህል ሲገዙ ሀብቷን በግላቸው በለጸጉበት እንጂ እነዚህንና ሌሎችንም የሕዝብ ፍላጎቶች አላሟሉም፤ ወደፊትም አያሟሉም፡፡ የሀገሪቱን ሀብትና የመንግሥቱን መዋቅር ለእነሱ አገልግሎት ያደረጉት ለሕዝብ ከፍርፋሪ በቀር ምንም ሳያስተርፉለት ነው፡፡ ሕዝቡ እነዚህን የሕዝብ ጠላቶች ሲሆን በውድ አለዚያም በግድ

አሰናብቶ ለሕዝብ የሚገዛና የሕዝብ ጥቅም የሚጠብቅ፥ የሕዝብ መብት የሚያስከብር መንግሥት ማቋቋም አለበት።

***ምን ዓይነት ትግል***

*ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሰጡት ጠላትን በአካል የሚታገሉ ወይም እነሱ ዘዴ የሚጠይቁት ሰው መሆን አለበት፤ ያልተጠየቀ አይመክርም፥ አይሽመግልም። ግን ምንም ዓይነት ትግል ቢታሰብ ምኞትን እውን በማድረግ በክተት ደረጃ መካሄድ እንዳለበት እገምታለሁ። ክተት ማለት፥*

> *ኢትዮጵያ ከሀገር-በቀል ጠላት ክራንቻ ውስጥ ገብታለች፤ ሀገሬ ናት የምትል ሁሉ*
> *እናት ሀገርህን ነፃ አውጥተህ በነፃ ለመኖርን ወንድ ሴት ሳትል ባንድነት ሆ! ብለህ ተነሣ*

*ማለት ነው። ተነሣ ማለትም "ጦር አንሣ አታንሣ" የሚል ትርጉም አያጠቃልልም። እሱን የሚወስኑት ታጋዮቹ ናቸው። የሌሎቻችን ግዴታ ታጋዮቻችን የወሰኑትን አዲሱን ትግል ሳናቅማማ መቀበል ነው። **አዲሱን ትግል በአንድነት ስናካሂድ መንግሥት የሚያከብረውን የትግል ሕግ እናከብራለን፤ መንግሥት የሚጥሰውን ሕግ የማክበር ግዴታ የለብንም።** ጠላት የጣሰውን ሕግ እያከበሩ መታገል ምንም ውጤት እንደማይኖረው ይኸው አየነው። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር የፈጸመብንን ወንጀል ዓለም በግልጽ ስላየና ስለኮነነው፥ መብታችንን ለማስከበር የምንወስደውን እርምጃ አይቃወምም። አንዱ ወገን መደንገፅ ሲሆን፥ ደንጋጩን እጅህን አጣምረህ ደንግጥ የሚል አይኖርም፤ ካለም ሰሚ ሊያገኝ አይገባውም። አልሞት ባይ ተጋዳይ ነው። ሀገራችንን ነፃ ለማውጣት ሁለተኛ የማይገኝ ዕድል ዛሬ እጃችን ላይ ወድቆልናል። በተሰጠው ዕድል የማይጠቀምን አምላክም ይርቀዋል።*

*ከላይ እንዳነሣሁት፥ ክተት ያንዳንድ ሰዎች ምኞት አይደለም። ኢትዮጵያ በትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር እጅ ከወደቀች ጀምሮ፥ የተነገረ ነው። በተለይም ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፈጸመው ወንጀል ለነፃነቱ ተቆርቋሪውን ሁሉ የሚያስተባብር ድምፅ ሆኗል፤ እኔም ሰምቸዋለሁ። ተቀብየም አስተጋባዋለሁ፤ ኢትዮጵያን አዲስ ዓለም፥ አዲስ ሀገር ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ሁሉ በቻልኩበት ቦታም እሰለፋለሁ፤ ምክንያቱም፤*

*የክተት ዓዋጅ ሀገር ማዳንንና ለሕዝቧ ሙሉ ነፃነት ማስገኘትን ዓላማው ያደርጋል።*

*የክተት ዓዋጅ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውንና የድዮስጶራውን ሕዝብ አንድ ወገን ያደርጋል።*

*የክተት ዓዋጅ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የጾታ፥ የእድሜ፥ የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነትን ለጊዜው ያስረሳል።*

*የክተት ዓዋጅ ኢትዮጵያን በጠላቶቿ ፊት ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ያደርጋል።*

*የክተት ዓዋጅ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ያዋረደውን የኢትዮጵያን ክብር ይመልሳል።*

*የክተት ዓዋጅ በሀገሪቱ ድምበር የጠላት ነፋስ የማያሳልፍ በሲሚንቶ የተማገረ አጥር ይሆናል።*

***የክተት እድሜና መዋቅር***

*ምንም ዓይነት ትግል ቢታሰብ የክተት እድሜው ነፃነት እስኪገኝ ድረስ ብቻ ይሆናል። የከተተ ሕዝብ ከዘመቻ መልስ ወደየሞያውና ወደየሥራው እንደሚሠማራ በአለፉት የክተት ዘመቻዎች*

ከሆነው አይተናል፡፡  የክተቱ ሠራዊቱ ሀገሪቱን ከጠላት ነፃ ካወጣ በኋላ አስተዳደሩን ለማን ትቶ ነው ወደየሥራው የሚመለሰው?

የክተቱ ትግል በተለያዩ ቡድኖችና በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ ዘዴዎች መካሄድ እንዳለበት እገምታለሁ፡፡ ግን ከአጀማመሩ እንዳይበላሽ፥ መጨረሻውም ውዥምብር እንዳይሆን፥ የእያንዳንዱ ቡድን መሪ የተለመደውን "ኑ በእኔ ቡድን ስር እንሰባሰብ" ማለቱን ትቶ፥ ሀገሪቱን ከወያኔ ፋሺስት አላቅቀው ዲሚክራሲን ለማስፈን በጋራ በመሠረቱት በአንድነት አንድ የፖለቲካ ማእከል ሲያቋቁሙና ለማእከሉ መሪ ተገዢ መሆናቸውን በመሐላ ቃል ሲገቡ ይታየኛል፡፡ ተባብሮ መሥራት የቱን ያህል እንደሚጠቅም የ97ቱ ቅንጅት አስተምሮናል፡፡ የሚያቋቁሙት ማእከል ጊዜያዊ አመራር ሆኖ ሀገሪቷ ነፃ እስክትወጣ ድረስ ትግሉን ያስተባብራል፡፡ ተገድዶ ለጠላት ይገዛ የነበረው የጦር ሠራዊት ዕድል አግኝቶ ወደ አገር አድኑ ክተት ሲመጣ፥ አመራሩ የኢትዮጵያን የመከላከያ ኀይል ይመሠርትበታል፡፡ ሠራዊቱ ጠላትን እየተወ መምጣቱ አይቀርም፤ በኢጣሊያ ፋሺስቶች አገዛዝ ጊዜ ባንዶች ዕድል ሲያገኙ ወደአርበኞች እንደመጡ እናስታውሳለን፡፡ ሀገሪቷ ነፃ ስትሆን፥ ጊዜያዊው አመራር የፖለቲካ ፓርቲዎች ተዘጋጅተው፥ ተወዳድረው፥ ያሸነፈው ፓርቲ ስልጣን እስኪይዝ ድረስ ሀገሪቱን ያስተዳድራል፡፡

## ለክተት አዋቃሪዎች ማስታወሻ

በአሁኑ ሰዓት ስለአወቃቀሩ ከማስበው ላይ ከዚህ የበለጠ ልናገርለት አልፈልግም፡፡ ሆኖም ክተትን የሚያዋቅሩትንና የሚያዘምቱትን አንድ ጠቃሚ ነገር ላስታውሳቸው ግዴታ ይሰማኛል፡፡ ስለሀገር በማሰብና በመጨነቅ፥ ስላገር ሁኔታ በማወቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉትና በድዮስጶራ በምንኖረው ዲሞክራሲ ናፋቂ ኢትዮጵያውያን መካከል ምንም ልዩነት የለም፡፡ ታጋዮቹ እኛን፥ "ስንት ሺ ኪሎ ሜትር ሆናችሁ እዚህ ጠላትን ፊት ለፊት የምንታገለውን በጋዜጣና በሬዲዮ አትምከሩን" ብትሉ የሚገባችሁ መሆኑን እናውቃለን፤ በዜና ረገድ ግን የማይታወቅ ነገር ሲኖር ያወቀ ላላወቀ እያሳወቀ እንረዳዳ እንጂ፥ "ስንት ሺ ኪሎ ሜትር ርቃችሁ እዚህ እማህሉ ላለነው አትንገሩን" ልትሉን አይገባም፡፡ ሳታሰልሡ የምታዳምጧቸው እነ ቢቢሲ፥ ቪኦኤ፥ ዶቼ ቬሌ ያሉት ድዮስጶራው ባለበት ዓለም ነው፡፡ አበክራችሁ የምታነቧቸው የአምነስቲ ኢንተርናሽናል፥ የሂዩማን ራይት ዋች፥ የኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ መግለጫዎች የሚወጡት እወዲህ ማዶ ባሉ ድርጅቶች ነው፤ ምናልባትም እውነቱን እንዲያወጡ ድዮስጶራው ውትወታ ሳያበዛባቸው አልቀረ ይሆናል፡፡

## የድዮስጶራው ሕዝብ በክተቱ ዘመቻ

በድዮስጶራ በሚኖሩት ነፃነት ወዳድ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ታጋዮች መካከል ምንም ልዩነት የለም ከተባላ፥ የድዮስጶራው ሕዝብም የክተቱ ሙሉ ተሳታፊ መሆን አለበት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ታጋዮች ለመክተት ምናልባት ጊዜ ሊወስድባቸው ስለሚችል እነሱን አንጠብቅም፡፡ ዛሬውኑ እንከታለን፡፡ እንዲያውም የኛ ከትቶ መገኘት እንዲከቱ ይገፋፉቸዋል፡፡ ድዮስጶራው በምን ዓይነት መክተት አለበት? የዚህ ሕዝብ አካል ስለሆንኩ መልስ ብሰጥ አያስቀይምብኝም፡፡

ቅንጅት ከፈረሰ ወዲህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተመልሰው ወደብዙነታቸው ስለሄዱ፥ እኛም እነሱን ተከትለን በዝተናል፤ አሁን ይኸንን ብዙነት በምንም መንገድ አስቀርተን አንድ ድርጅት ማቋቋም አለብን፡፡ በአካል የሚታገሉ "አንድ የፖለቲካ ማእከል አቋቁመው ለማእከሉ መሪ ተገዢ መሆናቸውን በመሐላ ቃል ሲገቡ" እንደታየኝ፥ በየሀገሩ ያለው ድዮስጶራውም በያለበት ሀገር አንድ አንድ ቡድን ሆኖ ራሱ በመረጠው አንድ ሸንጎ ይሰባሰባል፡፡ የየሀገሩ ሸንጎዎች "ተገናኝተው"

መማክርትና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቲ ያለበት የበላይ አስተባባሪ ባላደራ ቦርድ (የሸንጎዎች ሸንጎ) ይመሠርታሉ፤ መተዳደሪያቸውን አውጥተው ሥራ ተከፋፍለው ይመሩናል።

ድዮስጶራው የሸንጎ አባላቱን እንዴት ነው የሚመርጠው? የድዮስጶራውን ዓለም ለጊዜው ከሦስት ልክፈለው፤ ክተት አውሮፓ፥ ክተት ካናዳ፥ ክተት አሜሪካ። በሦስቱ አህጉር የኢንተርኔት ሙያ ያላችሁ ለየሀገራችሁ ሦስት ሰዎች የአስጠቋሚ ቡድን እንድትሆኑ ስማችሁን ስጡ። እየጠበቅናችሁ ነው፤ አታስጠብቁን። እነዚህ ቡድኖች ሕዝቡ የሸንጎ አባል እንዲሆኑ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ስም የሚሰጥበትን ሰሌዳ ይፈጥራሉ። (በኢንተርኔት አንዳንድ ጊዜ አቤቱታ (petition) ተዘጋጅቶልን እንደምንፈርም ማለት ነው።) ሰሌዳውን ሲያዘጋጁልን እያንዳንዳችን ማንነታችንን በማያጠራጥር ሁኔታ እያሳወቅን፥ ሊመሩን ብቃት አላቸው የምንላቸውን የሦስት ሰዎች ስም እንጠቁማለን። ሰሌዳው ከወጣበት ቀን አንሥቶ አንድ ሙሉ ወር ለጥቆማ ክፍት ይሆናል። መቸም የወያኔ ደጋፊዎች ስማቸውን የሚያቀርቡላቸው በብዛት እንዳሉ ሊገመት ይቻላል። ሆኖም የጠቋሚው ቡድን አባላት አብረውን የኖሩ፥ ስንዴውን ከእንክርዳድ መለየት የሚችሉ ናቸው። ብዙ ድምፅ ከአገኙት ውስጥ ዓሥራ አምስቱን መርጠን እንዲመሩን እንጠይቃቸዋለን። ስንጠይቃቸው፥ ሕዝቡን፥ በተለይ እንደኔ ያሉትን ሽማግሌዎች፥ “ድጋፋችሁ፥ ጸሎታችሁ፥ ቡራኬያችሁ አይለየኝ” ብለው ይቀበላሉ እንጂ የሕዝብ ጥሪ እምቢ አይባልም። እያንዳንዱ የድዮስጶራ ሸንጎ አባል ወርኃዊ መዋጮውን እንደሌሎቹ ወርኃዊ ዕዳዎቹ በቀጥታ ለሸንጎው ይልካል። ከክፍያ ወደኋላ እንዳይቀር አስታዋሹ ፍቅረ ነፃነት ነው።

**መደምደሚያ**

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር እየሰረሰረ በእናት ሀገራችን ላይ ያደረሰው ጉዳት ተጽፎ አያልቅም። ቢያልቅም መጻፉ ብቻውን አቃጥላ የምትፈጀንን አንድ እግር በርበሬ አይቀነጥስልንም። ከወያኔ ጭቆና ነፃ የሚያወጣን የክተት ትግል ብቻ ነው። ታግሎ ድል መቀዳጀት ለኢትዮጵያውያን አዲስ ነገር አይደለም። የምንነሣው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተነፈገውን የነፃነት መንግሥት ለማስገኘት፥ ከእነኔቶች አገዛዝ ነፃ ለመውጣት፥ ጥቂቶችን ብቻ የሚሊዮን ጌታ ለማድረግ ሳይሆን የሕዝቡን ሁሉ የኢኮኖሚ ደረጃ ከፍ ለማድረግ በሆደ ሰፊነትና በቈራጥነት ስለ ሆነ እናሸንፋለን። እናታችንን ለያዛት በሽታ ከክተት ሌላ መድኃኒት የለም። ሁሉንም አይተነዋል፤ ምኞታችንን እውን ለማድረግ አማራጩ ክተት ነው። ለኢትዮጵያ የሚጸልዩ አብያተ ክርስቲያናትና መስጊዶች የክተቱን ጥሪ እንዲጸልዩበትና ምእመናኖቻቸውን ወደክተቱ በጸሎት እንዲሸኟቸው እጠይቃለሁ።

ካሁን በፊት ብዙ ጊዜ የኅብረት ሐሳብ ቀርቧል፤ ጥሪውን የሚያብራሩ ልብ ማራኪ የንግግር ፈሊጦችም ተፈጥረዋል፤ “ያልተባበረ ተሰባበረ”፤ “ዛሬ ትብብር፥ ነገ ውድድር”፤ “እኛ ካልሆንን ማ?” ”ዛሬ ካልሆነ መቼ?” የሚሉት አገላለጾች ከማይረሱት ፈሊጦች ውስጥ አንዳንዶቹ ናቸው። ግን ሐሳቡ ሥነ ጽሑፋችንን አዳበረው እንጂ፥ እኛን ከቆምንበት አላነቃነቀንም። አሁን ግን ግንቦት 15 ቀን ሐሳባችንን በሥራ ላይ እንድናውል እንደወሰነልን ይታየኛል። የዛሬውን ድርሰቴን ያቀነባበርኩት ቀጣዩን እርምጃ የሚያቀጣጥል ክብሪት ለመጫር ነው። በኋላ እንዳይቈጨን፥ ለዛሬው ድል ያበቁንን የተቃዋሚ ድርጅቶችን እያመሰገንን፥ ዛሬውኑ መሠረቱን ለመጣል እንሽቀዳደም። ለማንኛውም ቀድመው በደረሱት  እንጀምራለን።  ካሁን በኋላ ሰንካላ ምክንያት እየፈለገ የማይተባበር “ኅብረት አጣን” ቢል እንደበፊቱ አያምርበትም። ካለ የሚወቀሰው ራሱን ነው። የኅብረት ምስጢሩ የኅብረት ጥሪ መቀበል ነው። ፈረሱም ይኸው፤ ሜዳውም ይኸው!!

**ድል ለኢትዮጵያ፥ ሙሉ ነፃነትና ክብር ለኢትዮጵያ ሕዝብ።**